# የኢትዮጵያ ሚና በሶማሊያ ሰላም

ሰለሞን ሽፈራው 04-18-17

በአፍሪካ ቀኝ አገዛዝ ታሪክ ከተስተዋሉ አሳዛኝ ክስተቶች መካከል ሶማሊያን ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ መንግስት አልባ ሆና እንድትቆይ ያደረጋት ቀውስ አንዱ ነው፡፡ ጎረቤት ሀገር ሶማሊያ ከ1982ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ጎሳን መሰረት ባደረገ አለመግባባት ምክንያት በተፈጠረ የእርስ በእርስ ትርምስ ከጊዜ ወደ ጊዜ ተባብሶ ሊቀጥል በመቻሉ፤ የቀድሞዋ ሶማሊያ ሪፐብሊክ ወደ በርካታ ትንንሽ ግዛቶች እንድትቀየር ያደረጋትን አደጋ መከሰቱ የሚዘነጋ ጉዳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያን በድንበር የምታዋስናት ጎረቤት ሀገር ያለአንዳች ማዕከላዊ መንግስት በቆየችባቸው በርካታ ዓመታት ውስጥ ከየትኛውም የዓለማችን ጥግ የሚመጡ ሽብር ፈጣሪ ቡድኖች፤ እንዲሁም ደግሞ ግለሰቦች እንዳሻቸው የሚፈነጩባት የድንበር ዘለለሎች መዳረሻ ወደ መሆን ተለውጣ ነበር፡፡ የሶማሊያ ቀውስ እየተባባሰ መጥቶ ሶማሊያውያን ለአስከፊ ፈርጀ ብዙ የህልውና ፈተና ተዳርገው፤ መላውን ዓለም አንገት ባስደፋ መልኩ በግፍ መሰደድን ብቸኛ አማራጭ ሆኖ ቆይተዋል፡፡ ይህ እጅግ በጣም አሳዛኝ ገፅታን በተላበሰ መልኩ የሚገለጽ ቀውስ በጎረቤቶቻችን ላይ ያስከተለና ጦሱ ለኛም ጭምር የሚተርፍ ስለነበረ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ዘለቄታዊ መፍትሔ በመፈለግ ረገድ ታሪክ የማይዘነጋውን አወንታዊ ሚና ተጫውቷል፡፡

መላው ዓለም ተስፋ ቆርጦ ሊተወው በመቻሉ ምክንያት ለሶማሊያውያኑ ፖለቲካዊ ቀውስ ዘላቂ መፍትሔ ሊፈለግለት ይገባል የሚል ፅኑ አቋም ይዞ የተነሳው ኢትዮጵያ መንግስት፤ ሶማሊያውያኑ እርስ በእርስ ከመናቆር ይልቅ የጋራ ህልውናቸው መሰረት የሆነችውን ሀገራቸውን ከገጠማት የብተና አደጋ ስለመታደግ ቆም ብለው ማሰብ እንደሚጠበቅባቸው ሳይገነዘቡ እንዳልቀሩ በቅርብ የሚታዘቡ የፖለቲካ ተንታኞች ከሚሰጡት ምስክርነት መረዳት ይቻላል፡፡ ለዚህ የተሻለ አብነት ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ለረጅም ጊዜ አሜሪካ ውስጥ በስደት እንደኖሩ የሚነገርላቸውና የጣምራ ዜግነትን ያገኙት፤ የአሁኑ የሶማሊያ ማዕከላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት መሐመድ አብዱላሂ መሐመድ (ኮርማጆ) ወደ የትውልድ ሀገራቸው ተመልሰው ፖለቲካውን የተቀላቀሉት ሁኔታን መመልከት ተገቢ ነው፡፡

ምክንያቱም ፕሬዝዳንቱ ዛሬ ላይ የሶማሊያውያን ለመመረጥ ያበቃቸውን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የጀመሩት፤ በተለይም ኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተችበት ያለው "ኢ.ሚ.ሶ.ም" የተሰኘ እንደ ኬንያ፤ ኡጋንዳና ጅቡቲን የመሳሰሉት ሌሎች ጎረቤት ሀገራት አጣምሮ የያዘ አህጉር አቀፍ የሰላም አስከባሪ ሰራዊት ወደ ሶማሊያ ዘምቶ ያቺን መንግስት አልባ ሀገር የዓለም አቀፍ ሽብርተኞች መፈንጫ ሆና ከመቅረት ለመታደግ ያለመ ጥረቱን መጀመሩን ተከትሎ በሰፈነው አንፃራዊ መረጋጋት ተነሳስተው እንደነበር የሚታመን ነው ፡፡ በሌላ አገላለጽ ሀገራችን ኢትዮጵያ የጎረቤት ሶማሊያን የተወሳሰበ ፖለቲካዊ ቀውስ በራሳቸው በሶማሊያ ህዝቦች ስምምነት መፍታት የማይቻልበት ምክንያት አይኖርም የሚል ጽኑ አቋም በመያዝ ጠፍቶ የቆየውን ሰላምና መረጋጋት ዳግም የመመለስ ጥረቷን አበክራ ከመጀመሯም ባሻገር፤ ሌሎች የኢ.ጋድ አባል ሀገራት ለጉዳዩ ዘላቂ መፍትሔ የማፈላለግ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት እንዲወስኑ የሚጋብዝ ቅድመ ሁኔታን በማሟላት ረገድ ያሳየችው ተነሳሽነት የሚዘነጋው አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ሚና እንደመሐመድ አብዱላሂ መሐመድ (ኮርማጆ) ዓይነቶቹ ትውልደ ሶማሊያውያን ዲያስፖራ ምሁራን ጭምር ሀገራቸውን ከፍፁም ጥፋት ለማዳን የየራሳቸውን በጎ አስተዋፅዖ ስለማበርከት እንዲያስቡ የሚያስገድድ አወንታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ችሏል ቢባል ከእውነት ከማጎላት የዘላለ አይሆንም፡፡

ይህ የሚያሳየው ማንኛውም ሰው ተወልዶ ያደገበትን ቤት በእሳት ቃጠሎ የመጋየት ክፉ ዕጣ ገጥሞት፤ የጎረቤት ሰዎች እርሱን ከቃጠሎው አደጋ ለመታደግ ሲረባረቡ ብናይ እኛም ከጎናቸው ለመቆም የማንገደድበት ምክንያት ይኖራል ብሎ ማሰብ ይከብዳልና ነው፡፡ ስለዚህም የአፍሪካ ቀንዷ ጎረቤት ሀገር የቀድሞዋ ሶማሊያ ሪፐብሊክ፤ ፕሬዝዳንት መሐመድ ዚያድ ባሬን በመሳሰሉ አምባገነን መሪዎቿ ምክንያት፤ ከኢትዮጵያውያን ጋር አላስፈላጊ የድንበር ይገባኛል ጦርነት ገጥማ ለመስፋፋት በሞከረችበት አንድ የታሪክ አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ሀገራችን ይህንን መጥፎ ጠባሳ በማያሻማ መልኩ የሚያክምና የቂም ሰንኮፉ ተነቅሎ እንዲሽር ሊያደርግ የሚችል ወንድማማችነትን ያሳየችበትን የሰላም ማስከበር ተግባርን ግንባር ቀደም ሚና ተወጥታበታለች ፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሶማሊያውያን የፖለቲካ ተንታኞች የአሁኑን የሶማሊያ ማዕከላዊ መንግስት በፕሬዝዳንትነት እንዲመሩ ከአንድ ወር በፊት የተመረጡት መሐመድ አብዱላሂ መሐመድ (ኮርማጆ) እንዳይመረጡ ኢትዮጵያ የእጅ አዙር ጫና ልትፈጥር

ትችላለች የሚል ስጋት ነበራቸው፡፡ ነገር ግን ግምታቸው ስህተት ሆኖ እንዳገኙት የገለፁ በወቅቱ ከጀርመን ድምጽ ሬዲዮ ጣቢያ (ዶ.ቼ.ቨ.ሌ) የአማርኛ ክፍል ጋር ባደረጉት ቆይታ ሚዛናዊ ምስክርነት ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም ሌላ አንድ አሁን ስማቸውን የዘነጋሁት የሶማሊያንና አጠቃላይ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትን ፖለቲካዊ እውነታ የሚመለከቱ ጥናትና ምርምር በማድረግ የሚታወቁ የቀጣናው ተንታኝ፤ ለኬንያ ናይሮቢ ሬዲዮ ጣቢያ በሰጡት ማብራሪያ ኢትዮጵያ በጉዳዩ ዙሪያ እየተጫወተች ያለውን አወንታዊ ሚና ያገናዘበ እንደነበር የሚታወስ ነው ፡፡

"እውነት ለመናገር በሶማሊያው ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ የተገኘው ውጤት እምብዛም ያልተጠበቀና የኔን ጥናታዊ ቅድመ ትንበያ ያከሸፈ ነው" ሲሉ ከሬዲዮ ጣቢያው ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ መስጠት የጀመሩት ናይሮቢው ተንታኝ፤ የስሌት ስህተት የፈፀሙበትን ምክንያትም እንደሚከተለው አስረድተዋል "የሶማሊያን ጉዳይ ወደዚህ ደረጃ እንዲደርስ በማድረግ ረገድ ወሳኝ የሚባለውን አወንታዊ ሚና ከተጫወቱት የቀጠናው ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ ቀዳሚ ስፍራ እንደምትይዝ የሚያከራክር አይደለም" ያሉ ሲሆን "ይህንን እውነታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ኢትዮጵያ የምትደግፋቸው ወገኖች እንዲመረጡ ተፅእኖ ማሳደሯ አይቀርም የሚል ግምገማ ነበረኝ" ፡፡

ሌላው የአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካ ተንታኝ ምርጫው የእርሳቸው ጥናታዊ ቅድመ ትንበያ ስህተት መሆኑን የሚያረጋግጥ ተቃራኒ ውጤት የተገኘበት ሆኖ በመጠናቀቁ የተሰማቸውን ስሜት ሲገልጹ "የሶማሊያው ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ላይ መሐመድ አብዱላሂ መሐመድ አሸናፊ ሆነው መገኘታቸው የሚያረጋግጥልን ነገር ቢኖር፤ የኢትዮጵያ መንግስት በጉዳዩ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ተጽፅኖ ለመፍጠር አለመፈለጉንና የሶማሊያ ችግር በራሳቸው ውሳኔ ሊፈታ የሚችለው ነው የሚለውን አቋሙን እንደሚያከብር የሚያሳይ ይመስለኛል" በማለት ተናግረዋል ፡፡

ሌላኛው የዶ.ቼ.ቨ.ሌ እንግዳ ሆነው የቀረቡት የሞቃዲሾ ነዋሪ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር "በምርጫው ሂደት ኢትዮጵያ ጣልቃ ገብታ ተፅእኖ ብትፈጥር ኖሮ መሐመድ ኢብዱላሂ መሐመድ ፕሬዝዳንት ሆነው አይመረጡም ነበር የሚለውን አስተያየት እኔም እጋራዋለሁ" በማለት ለዚህ አቋማቸው ያቀረቡት ምክንያትም "ለኢትዮጵያ ኃይሎች የተሻለ ቅርበትና የድጋፍ ስሜት እንዳላቸው የሚገምቱት ከምርጫው በፊት የሶማሊያ ጊዜያዊ መንግስት ፕሬዝዳንትነቱን ስልጣን ይዘው የቆዩት ሰው እንጂ መሐመድ አብዱላሂ

አይደሉምና ነው" የሚል ነበር፡፡ ሌላው ሁለቱም አስተያየት ሰጪዎች የተሰማሙት ቁልፍ ነጥብ ደግሞ "አዲስ ተመራጩ የሶማሊያ ፕሬዝዳንት የሚጠብቃቸውን ፈተና ሁሉ ተጋፍጠው ሀገራቸውን በሁለት እግሯ እንድትቆም ማድረግ እስከሚችሉ ድረስ የተለመደው የኢትዮጵያና የሌሎቹም ጎረቤት ሀገራት ድጋፍ በእጅጉ እንደሚያስፈልጋቸው መዘንጋት የለበትም" የሚል እንደነበር ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡

የአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካ ተንታኝ ምሁራን በተለይም "አል-ሸባብ" የተሰኘውን የሽብር ቡድን የመሳሰሉ የጥፋት ኃይሎች ጎረቤት ሶማሊያ ውስጥ የሚያደርጉትን መፈንጫ ሆና እንድትቀጥል ለማድረግ ያለመ አፍራሽ እንቅስቃሴ ከግምት በማስገባት እንደሆነ መገለፁም የሚታወስ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህም ረጅም ጊዜ ያለምንም ማዕከላዊ መንግስት በቆየችው ጎረቤት ሶማሊያ ውስጥ ደብዛው ጠፍቶ የነበረውን ሰላምና መረጋጋት ለማምጣት ሲባል ከሚደረገው ፈርጀ ብዙ ቀጣናዊ ጥረት አኳያ ኢትዮጵያ የመሪ ተዋናይነትን ስፍራ የሚያሰጣትን አወንታዊ ሚና የተጫወተች የኢ..ጋ.ድ አባል ሀገር ናት ብለን ብናጠቃልል ከተጨባጩ እውነት ነው፡፡ የሶማሊያን ቀውስ የመፍታት ጉዳይ በዓለም ማህበረሰብ ዘንድም ጭምር "ፈጽሞ የማይቻል" ተደርጎ በተቆጠረበት ከዛሬ አስር ዓመት በፊት ጀምራ ሰራዊቷን ወደዚያች ጎረቤት ሀገር በመላክ አሳዛኙን ሁኔታ ለመቀልበስ ያለመ የሰላም ማስከበር ተግባር ላይ የተሰማራቺው ኢትዮጵያ፤ የሶማሊያ ህዝብ ጎን በመቆም ረገድ ያሳየችው ቁርጠኝነት፤ ሌሎቹን የኢ..ጋ.ድ አባል ሀገራትም ወታደሮቻቸውን እንዲያዋጡና ሰልፉን እንዲቀላቀሉ ያስገደደ አወንታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ ሲታሰብ፤ በእርግጥም ሚናዋን የላቀ ሆኖ እንዲገኝ ያደርገዋል፡፡

ከ1998 ዓ.ም መጀመሪያ አንስታ ሶማሊያውያንን ስር በሰደደ የእርስ በርስ ግጭት ምክንያት ተወሳስቦ የቆየ ፖለቲካዊ ችግር ለመፍታት የሚያስችል ፈርጀ ብዙ ጥረት ያደረገችበት ግንባር ቀደም ሚናዋ ፤ ጉዳዩን ተስፋ አስቆራጭ እንደሆነ አድርጎ ወስዶት በነበረው ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ አድናቆት እንደተቸራት በር መክፈቱ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በዚያች ጎረቤት የቀውሱ ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሽ የመሆን ዕጣ የገጠመው የሶማሊያ ሰላም ወዳድ ህዝብ፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ህዝቦች በክፉ ቀን ከጎኑ ቆመን አለኝታነታችንን የምንገልፀለት ወንድሞቹ እንጂ፤ በምንም መልኩ ቢታይ የተለየ ዓላማ ሊኖረን እንደማይችል የተገነዘበበት የታሪክ አጋጣሚ መሆኑን ሚዛን ይደፋል ባይ ነኝ ፡፡

በተለይም የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ሰራዊት ወደ ሶማሊያ ከዘመተ ጊዜ ጀምሮ ለሀገሬው ህዝብ ደህንነት ሲል ራሱን ለመስዋዕትነት አሳልፎ ከመስጠት ቅንጣት ያህል እንኳን የማያመነታ ሆኖ እንዳገኙት እየገለፁ ለወታደሮቻችን ልባዊ ምስጋናቸውን ሲያቀርቡላቸው የሚደመጡ ሶማሊያውያንን በተለያዩ ሚዲያዎች መስማት የተለመደ ጉዳይ ስለሆነም ጭምር ነው፡፡ በአ.ሚ.ሶ.ም ጥላ ስር የታቀፉትም ሆኑ ከአ.ሚ.ሶ.ም ውጭ ራሱን ችሎ ሶማሊያ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ሰራዊት አባላት፣ ከሽብርተኛው የአልሸባብ ቡድን ጋር የሞት ሽረት ትግል እየገጠሙ የህይወት መስዋዕትነት ሲከፍሉ በዓይናቸው በብረቱ ደጋግመው ስለማየታቸው ምስክርነት የሚሰጡት የአካባቢው ነዋሪ ሶማሊያውያን ዜጎች፣ ወታደሮቻችን ለምን ሽብርተኞችን እየጣሉ መውደቅ እንደመረጡ ሊሰመርበት ይገባል ፡፡

ዋናው ቁምነገር የተከፈለውን ያህል መስዋዕትነት ተከፍሎም ቢሆን፣ ጎረቤት ሶማሊያ ከቀውስ ተላቀው የምናይበትን አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት ሊያስፍን የሚችል ፖለቲካዊ ቁመናን የያዘ ማዕከላዊ መንግስት መስርተዋል? ወይስ አልመሰረቱም? የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ይመስለኛል፡፡ ከዚህ አኳያ ለረጅም ጊዜ ሲራዘም ቆይቶ ከአንድ ወር በፊት በተካሄደው የሶማሊያውያን ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ፣ ሁሉንም ጎሳዎች በሚያስማማ የየአካባቢው ሀገር ሽማግሌዎች ውክልና አማካኝነት የተሰጠ ድምጽ መሐመድ አብዱላሂ መሐመድን  የሶማሊያ ማዕከላዊ መንግስት ርዕስ ብሔር አድርጎ እንደመረጣቸው አይዘነጋም፡፡

በሶማሊያውያን ፖለቲካዊ ታሪክ እንደሚታወቀው ፕሬዝዳንት የመሆን ስልጣን የሚሰጠው  በርካታ ቁጥር ያለውን ህብረተሰብ የሚወክል ተደርጎ ከሚወሰደው የሐውያ ጎሳ የሚወለድ መሆን አለበት ተብሎ ነበር፡፡ ነገር ግን የአሁኑ ምርጫ "ሀገራቸውን ከገባችበት ቀውስ የሚያወጣ አመራር ሊሰጥ የሚችለው ማነው?" በሚል ኃላፊነት ስሜት የተቃኘ ነው ተብሏል፡፡ በመሆኑም ተመራጩ ፕሬዝዳንት የመጀመሪያው የሐውያ ጎሳ ተወላጅ ሳይሆኑ ወደ የስልጣን ዕርከን የመምጣት ዕድል የገጠማቸው ሰው ናቸው፡፡

ፕሬዝዳንቱን በምርጫ እንዲያሸንፍ ያደረገው ምክንያት ጎሳን መሰረት ካደረገ አስተሳሰብ ይልቅ፣ ሁሉንም ሶማሊያውያን ህዝቦች በእኩል ዓይን የሚያዩ ሰው በመሆናቸው  እንደሆነ ምንጮች  ያመላክታሉ፡፡ ሶማሊያን የስርዓት አልበኝነት መፈንጫ አድርገዋት ከቆዩ ሃይሎች ጋር ምንም ዓይነት ድርድር አያስፈልግም በሚል አቋማቸውም

ጭምር እንደሚታወቁ የሚነገርላቸው አዲሱ ፕሬዝዳንት፤ ካለፈው መጋቢት 28 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ በአልሸባብ የሽብር ቡድን ላይ ብሔራዊ ጦርነት ማወጃቸውን ሚዲያዎች ዘግበዋል፡፡ እውን ይህ የሶማሊያው ፕሬዝዳንት መሐመድ አብዱላሂ መሀመድ ኮርማጆ የፀረ ሽብርተኝነት ዘመቻ የቀጣናችን ዋነኛ ስጋት ሆኖ የቆየውን የአልሸባብ ቡድን የጥፋት ተግባር እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ የሚያስቆም ውጤት ያስገኛልን? የሚለውን ጥያቄ ከወዲሁ መመለስ ባይቻልም ቅሉ፤ ጉዳዩ በዚህን ያህል መጠን ትኩረት ሲሰጠው ማየታችን በራሱ ግን ተስፋን የሚያጭር ነው፡፡